# ቅድስት ሥላሴ ቤተ ክርስቲያን በዮርዳኖስ /ኢያሪኮ/

ከጌታቸው በቀለ

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በእስራኤል ካሏት ጥንታውያን ገዳማት አድባራት አንዱ በኢያሪኮ ከተማ ጌታችን አምላካችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በተጠመቀበት በዮርዳኖስ ወንዝ አጠገብ በ1925 ዓ.ም በዳግርማዊት እቴጌ መነን ያሳነጹት ቅድስት ሥላሴ ቤተ ክርስቲያን ነው።

በዚህ ጽሑፍ ቤተ ክርስቲያኑ የሚገኝበትን የኢያሪኮን ከተማ፣ የዮርዳኖስን ወንዝና የቤተ ክርስቲያኑን ታሪክ በቅደም ተከተልን እንመለከታለን።

## ኢያሪኮ

ኢያሪኮ ዛሬ የፍልስጥኤማውያን ዋና ከተማ ሆናለች። የኢያሪኮ ጥንታዊው የአሮጌው ከተማ ፍርስራሽ በ1868 ዓ.ም በአርኬዎሎጂስቶች ጥናት ተቆፍሮ የአጥሩ ቅጽር መሠረት ተገኝቷል።

ኢያሪኮ ለብዙ ዘመን ተጐሳቁላ የምትታይ ከተማ ብትሆንም በአሁኑ ወቀት ወደ ዘመናዊነት እየተለወጠች ሄዳለች። ፍልስጥኤማውያን ከተረከቧትም ወዲህ አዲሷ ከተማ እየሰፋች፣ በርካታ ሕንፃዎች እየገነቡባት፣ የኢንዱስትሪና የልማት ዕቅድ እያስፋፉባት ይታያል። ከተማዋ በውስጧ ፍልስጥኤማውያን፣ የእስልምና እምነት ተከታዮች፣ በጥንት በመስቀላውያን ዘመን ከአፍሪካ አገሮች የመጡ ጥቁር አረቦች፣ ሌሎችም የክርስትና እምነት ተከታዮች የግብጽ ኦርቶዶክሳውያንና የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሁለት ገዳማት አሉባት።

የኢያሪኮ ከተማ የስምዋ ትርጉም በሦስት መልኩ ማየት እንችላለን።

1ኛ. በኢያሪኮ ከተማ ይኖሩ የነበሩ ከነዓናውያን የጨረቃ ሥዕል፤ ምስል አቁመው ያመልኩባት ነበርና «የጨረቃ አምላክ ከተማ» ትባል ነበር። በዕብራይስጥ «ያሬያህ» ወይም ያሪሆ ይሏታል ትርጉሙም «ጨረቃ» ማለት ነው።

2ኛ. የከተማይቱ ሰዎች የሽቱ ነጋዴዎች ነበሩና የመልካም ሽቱ አገር ናት ሲሉ ዐረቦች «ሪሃ» ይሏታል። ይኸም «ሽቱ» ማለታቸው ነው

3ኛ. ከቀረው ምድረ ከነዓን የበለጠ አምስት ዓይነት የተምር ዛፍና የብርቱካን ተክል የሚበቅልባት አገር ስለሆነች የአትክልት አገር ትባላለች። /ቅድስት ሀገር፤ ገጽ 107/

ኢያሪኮ እንደቀሩት የእስራኤል ከተሞች ሁሉ ታሪኳ ብዙ ነው። በእስራኤልና በፍልስጥኤም መካከል ስምምነት ስለተደረገ እ.ኤ.አ ከ1995 ዓ.ም ጀምሮ የፍልስጥኤማውያን መናገሻ ከተማ ሆናለች። በመጀመሪያ እስራኤላውያን ዮርዳኖስን ተሻግረው ገብተው ሳይወርሷት በፊት የከተማዋ ቅጥርና ምሽግ በግንብ ተጠናክሮ ተሠርቶ እንደነበር ከቅዱሳት መጻሕፍት እንረዳለን መጽሐፈ ኢያሱ ምዕ.2ና 6

እስራኤላውያን ኢያሪኮን የያዙት በሠራዊት ብዛት አልነበረም። ነገር ግን ከእግዚአብሔር ታዘው ሰባት ቀን ካህናቱ ታቦት ተሸክመው ሲዞሩ ሰንብተው በሰባተኛው ቀን በእግዚአብሔር ፈቃድና ኃይል ቅጽርዋና ምሽጓ ፈረሰ።

## የዮርዳኖስ ወንዝ /River Jordan/

የዮርዳኖስ ወንዝ ኢየሱስ ክርስቶስ የተጠመቀበት ከገዳመ ቆረንቶስ ወይንም ከኢያሪኮ ጥንታዊው ከተማ 10 ኪ.ሜ ያህል ይርቃል።

የዮርዳኖስ ወንዝ ከሦስት ተራሮች ሥር መንጭቶ ይፈሳል። አንደኛው ተራራ /Nahal Dan/ የሚነሣው ዳን /Dan/ ተብሎ የሚጠራው፤ ሁለተኛው ከአርሞንኤም ተራራ /Nahal Hermon/ የሚነሳው ባንያስ /Banias/ተብሎ የሚጠራው፤ ሦስተኛው ከሊባኖስ ተራሮች /Nahal ሰነፀረሐ የሚነሳው ሐስባኒ /Hasbani/ ተብለው ይጠራሉ፤ ከሰሜን ወደ ደቡብ ይፈሳሉ።

ሦስቱም ወንዞች ለየብቻቸው ስድስት ኪ.ሜ ተጉዘው «ሜሮን» /Lake Hula/ ከምትባል ሐይቅ ደርሰው ይገናኛሉ። አንድ በመሆን ሐይቁን አቋርጠው 17ኪ.ሜ ያህል ከተጓዙ በኋላ ከዋናው ገሊላ ባሕር ይቀላቀላሉ።

በዛሬው ዘመን የሦስቱ ምንጮች መነሻቸው በእስራኤል ይዞታ ክፍለ ሀገር ውስጥ ነው። ከገሊላ ባሕር በደቡብ ጫፍ የሚወርደው «የዮርዳኖስ ወንዝ» ተብሎ በሸለቆ ውስጥ 117 ኪ.ሜ ይጓዝና በሎጥ ባሕር «በጨው ባሕር» ውስጥ ሰጥሞ ይቀራል።

## ዮርዳኖስ በዘመነ ሐዲስ

በዘመነ ሐዲስም መጥምቀ መለኮት ቅዱስ ዮሐንስም ከሰው ተለይቶ በዮርዳኖስ በረሃ ሕዝበ እስራኤልን የንስሐ ጥምቀት እያጠመቀ ኖሯል። ኢየሱስ ክርስቶስ መምጣቱን ለሕዝበ እስራኤል አስተማረ፣ የንስሐ ጥምቀት በዮርዳኖስ እያጠመቀ «ጽድቅ ለመሥራት ተሰናዱ፤ መንግሥተ ሰማያት ለመግባት ንስሐ ግቡ» እያለ አዋጅ ነገረ። ኢሳ.40።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስም ከሰማየ ሰማያት ወርዶ፣ ከቅድስት ድንግል ማርያም ተወልዶ፣ ባጭር ቁመት በጠባብ ደረት ተወስኖ 30 ዓመት ሲሆነው በዮርዳኖስ ወንዝ፤ በዮሐንስ እጅ በትህትና ተጠመቀ።

መሲህነቱንና አምላክነቱን አስመሰከረ፤ ምስክርነቱም ከሰው አልነበረም ወይም በመልአክ አፍ አልተነገረም። ነገር ግን ከዘላለም ጀምሮ በባሕርይ አባቱ «በእርሱ ደስ የሚለኝ የምወደው ልጄ ይህ ነው» ብሎ መሰከረለት። ማቴ.3-17 መንፈስ ቅዱስም በርግብ አምሳል በላዩ አረፈበት።

በዚህ ምክንያት ክርስቲያን የሆኑ ሰዎች ሁሉ «ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የተጠመቀበት» ነው እያሉ በዮርዳኖስ ወንዝ እየወረዱ፤ ይጠመቃሉ። በዓመት አንድ ጊዜ ለበረከትም እያሉ ላልመጡ ዘመዶቻቸው ለማካፈል ውኃ ቀድተው እየያዙ ይሄዳሉ። በዚህም አምላካቸው እግዚአብሔርን እያመሰገኑ ወደ ሀገራቸው ይመለሳሉ።

በየዓመቱ ጥር በባተ በ11ኛው ቀን የጥምቀት ዕለት ክርስቲያን የሆነ ሕዝብ ሁሉ ዮርዳኖስ እየወረዱ ይጠመቃሉ።

እስራኤል መላ ኢየሩሳሌምንና ዙሪያዋን ከተቆጣጠረችበት እ.ኤ.አ 1967 ዓ.ም ጀምሮ ወሰኗን በዮርዳኖስ መንግሥትና የእስራኤል መንግሥት የጦር ክልል አድርገው ፈንጂና ሌላም መከላከያ መሣሪያ ስላጠመዱበት መግባት አይቻልም፡፡

በባሕሩ ዳርቻ ግሪክ፣ አርመን፣ መስኮብ፣ ሶርያ ኮፕት ሌሎችም ቤተ ክርስቲያን ሠርተውበት ነበር፡፡ በዚህ በዮርዳኖስ ወንዝ ከግማሽ ጋሻ የሚበልጥ የኢትዮጵያ ቦታ ይገኛል፡፡ እቴጌ መነን በዮርዳኖስ ቅድስት ሥላሴ ስም ያሳነጹት ቤተ ክርስቲያንና ሰፊ ገዳም ነበር፡፡ ሁሉም በጦርነቱ ምክንያት ስለተለቀቀ ምድረ በዳ ሆኖ ቀርቷል፡፡ ቤተ ክርስቲያኑም በፈንጂ ተመትቶ ጉዳት ደርሶበታል፡፡

አሁን ከሰላሙ ማለትም እ.ኤ.አ ከ1995 ዓ.ም ወዲህ በሁለቱ አገሮች በዮርዳኖስና በእስራኤል መንግሥታት ስምምነት ስለተደረገ በዓመት አንድ ጊዜ ጥር 10 ቀን የሁሉም አብያተ ክርስቲያናት ምእመናን መሪዎቻቸው ሊቃነ ጳጳሳትን አጅበው ወደ ወንዙ እየወረዱ፣ ሥርዓተ ጸሎት በማድረስ በዓሉን ያከብራሉ ከውሃው ለበረከት ይጠመቃሉ፡፡

ወደ ኢያሪኮና ወደ ዮርዳኖሰ መውረጃ ያለው ዳገትና ቁልቁለት፤ አግድመት ለከብት ሣር፤ ለዓይን ማረፊያ ቅጠል ተፈልጎ አንዳች ነገር አይገኝበትም፡፡ በዮርዳኖስ ወንዝ ግን ዳርዳሩን ልዩ ልዩ ለምለም ቅጠል፤ አኪያ፤ ሸንበቆ፤ ግራር ሌላም ይህን የሚመሳስሉ፤ ለሰው ጥላ ለወፎች ከለላ የሚሆኑ ሞልቶበታል፡፡ የዮርዳኖስ ውሃ ሲያዩት ነጭና ድፍርስ ይመስላል፣ ሲጠጡት ግን ይጣፍጣል፡፡ ዓሣ በብዛት ይገኝበታል፡፡

ዮርዳኖስ ዮሐንስ ሲያጠምቅበት የነበረ ወንዝ ነው፡፡ ያጠመቀበት ቦታ ግን በተለየ ይኽ ነው፡፡ ወይም ከዚህ ወዲህ ነበር ተብሎ ሊታወቅ አይቻልም የሚሉ አሉ፡፡ «ዮሐንስ በምድረ በዳ ታየ» የሚለው የኢያሪኮን በረሃና ጌታም በዮርዳኖስ ተጠምቆ ወደ ገዳመ ቆንቶስ የወጣው በዚሁ መሆኑ አያጠራጥርም፡፡ መጻሕፍት ሁል ጊዜ «ምድረ በዳ» እያለ የሚያመላክቱት ወደ ኢያሪኮ ግድም ያለውን ነው፡፡

በኢያሪኮ ይኖሩ የነበሩ ሕዝበ ክርስቲያን በየዓመቱ ጥር 11 ቀን ወደ ዮርዳኖሰ እየወረዱ ሲጠመቁ ያዩ ቦታውም ይህ ነው እያሉ ሲያሳዩ የሰሙ የኢየሩሳሌም ተሳላሚዎች በ400-600 ዓ.ም በጻፉት ታሪክ አመልክተዋል፡፡ ይህም ልማድ እንደ ቆየ፣ ቦታውም ተለይቶ እንደታወቀ፤ ዘመኑም ሳይረዝም፣ ዝክሩ ሳይረሳ ከ1000 ዓመት ጀምሮ እስከ አሁን ከአባቶች ተያይዞ ወደ ልጅ ልጅ የወረደ ታሪክ ነው ይባላል፡፡

ግርማዊት እቴጌ መነን በሀገረ ቅድስት ኢየሩሳሌም ህያው የሆነ መታሰቢያ መሥርተው አልፈዋል፡፡ ግርማዊት እቴጌ መነን፤ ልዕልት ወ/ሮ መነን ሲባሉ በ1915 ዓ.ም ወደ ኢየሩሳሌም ሔደው ቅዱሳት መካናትን ተሳልመው በኢየሩሳሌም ገዳም ለሚገኙ ማኅበረ መነኮሳት የልብስ የምግብ፣ የገንዘብ ርዳታ አድርገዋል፡፡ ለአብያተ ክርስቲያናቱም ንዋየ ቅድሳት፣ አልባሳት አበርክተዋል፡፡

በብዙ ፈርጥ የተጌጠ አክሊላቸውን ሰጥተዋል፡፡ ይህን አክሊል በየዘመኑ የገዳሙ አስተዳዳሪዎች መምህራን መጋብያን፤ ዛሬም ጳጳሳት በዓበይት በዓላት ጊዜ እያደረጉ ያከብሩበታል፡፡

በ1925 ዓ.ም /በኢያሪኮ/ ዮርዳኖሰ ወንዝ ከመካነ ጥምቀቱ አጠገብ ታላቅ ቤተ ክርስቲያንና ቤተ ማኅበር የመነኮሳት መኖሪያ የሚሆን 12 ክፍልና ትልቅ ሳሎን፣ የምግብ ማብሰያና መጸዳጃ ያለው፤ በዘመናዊ ዕቅድ ካሳነጹ በኋላ በዓመቱ ወደ ኢየሩሳሌም በመምጣት ቤተ ክርስቲያኑን «በቅድስት ሥላሴ» ስም አስባርከው፤ ቅዳሴ ቤቱን አክብረው፤ ቤተ ማኅበሩን መርቀው ተመልሰዋል፡፡

ግርማዊት እቴጌ መነን በዚህ ብቻ ሳይወሰኑ በዮርዳኖስ ለሠሩት ቤተ ክርስቲያን ለሕንፃው መጠበቂያና በገዳሙ እያገለገሉ ለሚኖሩት ማኅበር መርጃ እንዲሆን አስበው በአዲስ አበባ አራዳ ጊዮርጊስ አጥቢያ «ለዮርዳኖስ ቅድስት ሥላሴ» ርስት አድርገው ስሙንም «ቤተ ዮርዳኖስ» ብለው አበርክተዋል፡፡ /ቅድስት ሀገር፤ ገጽ 196-179/

ወስብሐት ለእግዚአብሔር

**ማኅበረ ቅዱሳን**